# ትንቢተ ዳንኤል

Webinar 1
Introduction on the book of Daniel

ፓ/ር አስፋው በቀለ
www.operationezra.com

# ትንቢተ ዳንኤል

## መግቢያ

በውስጡ ለመረዳት አስቸጋሪ የሚመስሉ ነገሮች ቢኖሩበትም በትጋትና በጥንቃቄ ከተጠና ይሄ ነው የማይባል መለኮታዊ ምስጢራት የሞሉበ መጽሐፍ ነው። ለህይወት መርህ የሚሆኑ ትምህርቶችንና መገለጦችን በውስጡ ጠቅጥቆ የያዘው ትንቢተ ዳንኤል የዮሃንስ ራዕይን እንድናውቅ የሚረዳን ቁልፍ የትንቢት መጽሐፍ ነው። ትንቢተ ዳንኤል ስለዘመናትና በዝመናት ውስጥ ገና ሊከሰቱ ስላሉት ስለባቢሎናውያን፣ ስለፋርስና ሜዶንና ስለግሪክ መንግስታት መነሳትና መውደቅ ይተርካል። “አስቸጋሪ መጽሐፍ ነው” የሚለውን የሰነፎችን ቃል ሳንሰማ ቃሉን በትክክሉ በያይነቱ እየበለትን እንድንረዳው እግዚአብሔር ይርዳን።

Teaching on the book of Daniel

www.operationezra.com

Webinar every Friday from 5:45 till 6:45 p.m

Starts July 6th. 2012

This outline is free for all webinar attendants!





# ዳንኤልና ባቢሎን

## I. ዳንኤል ማነው?



1. ዳን + ኤል = ዳንኤል (ዳኛ + እግዚአብሔር = እግዚአብሔር ዳኛዬ ነው ማለት ነው።
2. ገና በወጣትነቱ በባቢሎን ተማርኮ የተወሰደ ምርኮኛ ነበር - ይህም ቀደም ብሎ የተነገረውን የኢሳያስን ትንቢት እንዲፈጸም ያደርገዋል (ኢሳ.39፡7፤ 2ነገ.20፡18)
3. በኢዮአቂም ዘመን በሆነው የባቢሎን ጥረዛ ወደ ባቢሎን ከተወሰዱት የንጉሳውያን ቤተሰብ አንዱ ነበር (1፡3፤6)
4. ዳንኤል በባቢሎን እንደደረሰ
   - ✓ የስም ለውጥ ተደረገለት ዳንኤል የሚለው ስም ተለውጦ “ብልጣሶር” ተባለ ትርጓሜውም “ቤል (የአማልክት ስም) ንጉሱን ይጠብቅ” እንደማለት ነው። (ቤል +ሻዘር)
   - ✓ የባቢሎንን ትምህርት እንዲማር ተደረገ - ስነከዋክብት (ኮከብ ቆጠር?)
   - ✓ የባቢሎንን ምግብ እንዲበላ ታዘዘ...ወዘተ..
5. በባእድ ምድር ለአምላኩ የታመነ ሰው ነበር
6. ምስጢራትን እንዲራዳ እግዚአብሔር ስጦታን ሰጥቶት ነበር
7. የጠቢባን ሁሉ አለቃ ሆኖ ተሹሞ ነበር።
8. የናቡከደናጾር የልጅ ልጅ የብልጣሶር ህልምን ሲተረጉም የበለጠ ሹመት ተሰጥቶት ነበር። (5)
9. ከብልጣሶር በኋላ በዳርዮስ ዘመን በመንግስት ውስጥ 3ተኛ. ሰው (ባለስልጣን) ነበረ፡፡ ም.6
10. ዳንኤል ከተንኮለኞች ወጥመድ አመለለጠ (ም.6)

11. የፋርስና የሜዶን ንጉስ ቂሮስ እስከሚነሳበት ዘመን ድረስ በባቢሎን ባለስልጣን ነበር (10፡1)
12. ምናልባት ከተመለሱት አይሁድ ጋር አልተመለሰም… በባቢሎን ሽምግሎ እዚያው ሞቶ ይሆናል።
13. ዳንኤል የተወደደና መልካም ስም ያለው ነቢይ ነበር፡-
    1. የነቢዩ ህዝቄል ዘመነኛ ነበር (ህዝ.14፡14፤28፡3)
    2. የኤርሚያስ ዘመነኛ ነበር (626-528)
    3. በያህዌ የተወደደ ነበር (10፡18-19)
    4. ገብርዔል የተወደድህ ብሎ ምስከረለት - 9፡20-23
    5. የአህዛብ ነገስታት የነበሩት ለዳንኤል አብሮት ነበራቸው፡_
        - ናቡከደነጾር - 2፡47
        - ብልጣሶር - 5፡29
        - ዳርዮስ - 6፡20፤26
    6. ጌታ ኢየሱስም ስሙን ጠቅሶ ተናግሯል - ማቴ.24፡15
    7. የዕብራውያን ጸሃፊም የእምነት ጀግና አድርጎ ጠግሶታል - ዕብ.11፡34



Webinar - July 6th.2012 – www.operationezra.com

1. ትንቢተ ዳንኤል መጽሐፍ -

    - ✓ በአራማይክና በዕብራይስጥ የተጻፈ ነበረ
    - ✓ ምዕራፍ 2 እስከ 7 በአራማይክ የተጻፈ ነው
    - ✓ ምዕራፍ 1 እና ምዕራፍ 8-12 በዕብራይስጥ የተጻፈ ነው

2. የትንቢተ ዳንኤል መልዕክት

    - ✓ እግዚአብሄር ሉዓላዊ አምላክ ነው
    - ✓ እግዚአብሔር የወደፊቱን አዋቂ ነው
    - ✓ በሰው ታሪክ መካከል እግዚአብሔር የበላይ ተቆጣጣሪ ነው
    - ✓ ከፉ ተሸናፊ እንጂ አሸናፊ አይደለም

## IV. የምርኮ ዘመናት

1ኛ ምርኮ
2ነገ.24፡1-4
(604-605)

2ኛ ምርኮ
2ነገ.24፡8-7
(597)

3ኛ ምርኮ
2ነገ.24፡18-25፡22)
587-586

V.

VI.



## VII. የትንቢት ዳንኤል መጽሐፍ

| | |
|---|---|
| ምዕራፍ 1 | መግቢያ (ዳንኤልና ጓደኞቹ በባቢሎን በንጉስ ደጅ) |
| ምዕራፍ 2 | የናቡከደነጾር ህልምና የዳንኤል ራዕይ፤ መለኮታዊ ፍርድ በአራቱ የምድር የመጨረሻ መንግስታት ላይ) |
| ምዕራፍ 3 | የናቡከደነጾር የወርቅ ምስል-ሦስቱ አይሁዶች በእሳት መጣላቸው |
| ምዕራፍ 4 | የናቡከደናጾር ህልም ስለታላቅ ዛፍና ትርጉሙ |
| ምዕራፍ 5 | የግድግዳው ጽሁፍ |
| ምዕራፍ 6 | የዳንኤል መሾምና የአንበሳ ጉድጓድ መጣል |
| ምዕራፍ 7 | የዳን ኤል ራዕይ ስለአራቱ የምድር ታላላቅ መንግስታት (የዮሃንስን ራዕይ ለመፍታት ቁልፍ) |
| ምዕራፍ 8 | የዳንኤል ራዕይ ስለ ግሪኩ መንግስት ስለታላቁ አሌክሳንደር መንግስት አራት ቦታ መሰንጠቅ |
| ምዕራፍ 9 | የዳንኤል ስለ መሲሁ ጉዳይ፤ |
| ምዕራፍ 10 | የግብጽና የሶርያ ውዝግብ የይሁዳም በሶርያ መገዛት |
| ምዕራፍ 11 | የሮማውያን መነሳት |
| ምዕራፍ 12 | የዘመን ፍጻሜና የክርስቶስ መምጣት) |



Webinar - July 6th.2012 – www.operationezra.com

## II. ባቢሎን በዳንኤል ዘመን



- ✓ ባቢሎን - ሽናር ወይንም ሰናዖር በመባል ይታወቅ ነበር (ዘፍ.10፡10፤ 11፡2፤ ኢሳ.11፡11)
- ✓ ባቢሎን - የከለዳውያን ምድር ተብሎም ይጠራ ነበር (ኤር..24፡4፤ ህዝ.12፡13)
- ✓ የስልጣኔ ምንጭ ነበረች
- ✓ በጤግሮስና በኤፍራጥስ ወንዞች የተከበበች ነበረች… ቀድሞ የኤደን ገነት (ዘፍ.2፡14) የነበረችበት አካባቢ ነበረች።
- ✓ ብዙ ህዝብ ይኖርባት የነበረች የአለም ታላቅ ከተማ ነበረች
- ✓ ባቢሎን በናቡከደነጾር ዘመን 200 ስኩዩር ማይል ስፋት ነበራት፤
- ✓ መንገዶቿ እንዳሁኑ ዘመን በአራት ማዕዘን ይጋጠሙ ነበር።
- ✓ 3 ወፍራም ግንብ ዙሪያዋን የታጠረች ነበረች…በግንቡ ላይ ወታደሮች በሰረገላ እየነዱ ከተማይቱን ይጠብቁ ነበር።
- ✓ በአለም ላይ ከሰባቱ አስደናቂ ነገሮች አንዱ ተብሎ የሚጠቀሰው ናቡከደናጾር ለሁለተኛ ሚስቱ ያሰራላት የደርብ መናፈሻ አለባት። (ዳን.4፡28-30 ያለውን ታሪክ ይመልከቱ)
- ✓ በስተመጨረሻም ባቢሎን በራዕይ መጽሐፍ የአለምና የርኩሰት…ምሳሌ አድርጎ ይመስላታል።
    - ○ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች…ራዕ.14፡8፤18፡2
    - ○ ታላቂቱ ባቢሎን ተብሎ የተጻፈባት …ራዕ.17፡5
    - ○ አሁን ሙሉ በሙሉ ተደምሥሳለች…የነቢይ የኢይሳያስ ትንቢትም ተፈጽሟል..(ኢሳ.13፡17-22

## III. የባቢሎን ኀይማኖቶች



- ✓ የአሶርና የባቢሎን አማልክት አንድ ናቸው
    - ✓ ጥንቆላ ወዳድ ህዝብ ነው
    - ✓ መርዱክ ፈጣሪ ኢአ ደግሞ “የውሃ መንፈስ” ብለው ያምኑ ነበር
- ✓ ባቢሎናውያና አማልክቶቻቸውን እጅግ ይፈሩ ነበር

i. ሁልጊዜ ህዝባቸው የሚጎድ እንደሆኑ ያምኑ ነበር::

ii. አምልክቶችን “የተዘጋ በር ሆነ የሙብረቅ ፍንዳታ አይከለክላቸውም እንደ እባብ በበሮች ስር እየተምዘገዘጉ በቤት መጋጠምያ ሁሉ እንደ ነፋስ መግባት ይችላሉ” ብለው ያምኑ ነበር *(Dorothy Mills, the book of the ancient world, p.105)*

iii. በጠንቋይና በአጋንንቶች ያምኑ ነበር፤ የሚያስፈራሯሯቸውን መናፍስት ለማባረር የተለያየ አሰፈሪ መልክ ያላቸው አማልክቶችን በቤታቸውን በየስፍራው ያስቀምጡ ነበር።

iv. በከዋክብት ኀይል ያምኑ ነበር

1. ኮከብ ቆጠራ አስትሮሎጂ የተወለደው በባቢሎን ነው።





2. የወደፊቱ ከከዋክብት ማወቅ ይቻላል ብለው ያምኑ ነበር

v. ለአምልክቶቻቸው ዝጉራት ተብሎ የሚሰራ መቅደስ ይሰሩ ነበር።

1. በሰባተኛው ቀን ያመልኩ ነበር
2. ከሞት በኋላ ህይወት አለ ብለው ያምናሉ ... አሰጨናቂና ጨፍጋጋ ህይወት ነው ያላሉ...ነፍስ የሚሄድበት ስፋራ “መመለሻ የለሽ ምድር” ብለው ይጠሩታል።
3. ኀይማኖታቸው ምግባራቸውን

